# በፍርድ አፈጻጸም ሂደት አከራካሪ የሆኑ ጭብጦች፣ለውይይት የቀረበ፣

1. የፍ/አፈፃፀም የመንግስት ዕዳ ለመሰብሰብ በህግ ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም።
   - በተግባር የመንግስት ግብርና ቀረጥ በቅድሚያ ይሰበሰባል
   - የአሰራሩ አግባብነት ፣ ግልፅነትና ምክንያት

   የትኛው የመንግስት ዕዳ የግድ መሰብሰብ አለበት
   - ቀረጥ
   - ታክስ - የካፒታል ዕድገት ጨምሮ?
   - ሊዝ ዕዳ --ውዝፍ ብቻ ወይስ ወደ ፊት ለረዥም ጊዜ የሚከፈል የሊዝ ዕዳ ይጨምራል?
2. የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ህጋዊ ሰውነት የሌለው፣የፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያስፈፅም የሥራ ክፍል መሆኑ እየታወቀና ግልጽ የሰበር ውሳኔ እያለ ለምን ፍ/ቤቶች የፍ/ር ክስ ተቀበለው ይወስናሉ? ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?
3. የሀራጅ አሸናፊ ተጫራች በ15 ቀን ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እንዳበት በህግ የተመለከተ ነው። ይሁንና የሚከተሉት አፈፃፀሞች ግልፅነት ይጎላቸዋል ፡፡
   - የ15 ቀን መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው ከጨረታ ቀን ወይስ ከሚቀጥለው ቀን ጀምሮ?
   - የሥራ ቀን ብቻ ነው የሚቆጠረው ወይስ የበዓላት ቀን ጨምሮ?
   - የፍርድ አፈፃፀም ሒሳብ ክፍል ምክንያት ገንዘቡ ገቢ ሳይደረግ በህግ የተመለከተው የ15 ቀን ካለፈ ምን ማድረግ ይቻላል? (ለምሳሌ) ሲፒዩ የተሰራው ከንግድ ባንክ አይደለም በሚል ወይም ገዢው ወራሽ ወይም የቀዳሚ መብት ተጠቃሚ ከሆነ ገቢ ማድረግ ያለበት ሒሳብ ተሰርቶ የራሱ ድርሻ ተቀንሶ ልዩነት ብቻ ወይስ አይደለም በሚል ጭቅጭቅ ከሆነስ ?
4. የቀዳሚነት የፍ/ቤት ትዕዛዝን የመብቱ ተጠቃሚዎች ማቅረብ ለባቸው ለፍ/አፈፃፀም መ/ቤት ወይም በቀጥታ በሀራዥ አዳራሽ ለሀራጅ ባይ? ፣ ማቅረብ ያለባቸው መቼ ነው?

   ሀ.በጨረታ ቀን የሐራጅ ሒደቱ ከመጠናቀቁ በፊት ወይስ ከሀራጅ ቀን በኋላም ቢሆን

   ለ.የሀራጅ ቀን ካለፈ በኋላ የሚቀርበው የቀዳሚነት መብት ተቀባይነት እንዴት ይታያል ?

   ሐ.ፍ/ቤቶች የጨረታ ቀኑን ባለማወቃቸው ጨረታ ካለፈ በኋላ የሚሰጥ የቀዳሚነት መብት ተቀባይነት እንዴት ይታያል፤
5. እያንዳንዱ የጨረታ ቀን ለፍ/ቤት ሪፓርት ሊደረግ ይገባል ወይስ አይገባም?
6. ቀዳሚነት መብት ጋር ተያይዘው የሚያጋጥሙ የትዕዛዝ ልዩነቶች እንዴት ወጥ ማድረግ እንችላለን

   ሀ.የቀዳሚነት መብት ለሁለቱ ባለመብቶች ሲሰጥና ግራቀኙ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ምን ማድረግ ይቻላል?

ለ.የቀዳሚነት መብት የተሰጣቸው ባለመብቶች የቀዳሚነት መብት ትተናል ሲሉ ዳኞች ሊሰጡ የሚገባቸው ትዕዛዞች ምን ቢሆን ይሻላል ?

ሐ.የቀዳሚነት መብት የተሰጣቸው ባለመብቶች መብቱን ትተናል ሲሉ እና ዳኞች የጨረታ አሸናፊው ንብረቱን ይግዛ (ይውሰድ) ብለው ሲያዙ ገዥውም በተለያየ ምክንያት ትቻለሁ (ገንዘቡን አጥፍቻለሁ ሌላ ንብረት ገዝቼበታለሁ ሲል የሚሰጠው ምክንያታዊ ትዛዝ ምን ሊሆን ይችላል? (የዳኞች ፍቃድ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ)

መ.በህግ የሚታወቀው ጨረታ ስንት ጊዜ ነው? የመጀመሪያ ጨረታ ድጋሚ ጨረታ ሌላ ጨረታ

ሠ.በሁለተኛ ጊዜ (ቀዳሚነት መብት የተሰጠው ሰው ገዥነት ትቻለሁ በማለቱና የጨረታ አሸናፊም ትቻለሁ በማለቱ የሚደረገው ሁለተኛ ጨረታ ድጋሚ ጨረታ ሊባል ይችላል ? ውጤቱስ ምን ይሆናል ?

ረ. አንዳንዴ በቂ ተጫራች አልቀረበም፣ ደላሎች ከአንዱ ወገን ጋር ተመሳጥረው ሊገቡ ነው ወይም ገብተዋል፣ጨረታው ሊጭበረበር ይችላል በማለት ጨረታው እንዳይካሄድ የፍርድ ባለመብቶች ሲቃወሙ ጨረታ ማቆም ይቻላል ወይስ መቀጠል አለበት? ማቆም አለበት የሚባል ከሆነስ ቀጣዩ ጨረታ ውጤቱ ምን ይሆናል? ድጋሚ ጨረታ ይባላል?

7. ይዞታው በከተማ አስተዳደሩ ህግ ለቀድሞ ተጋቢዎች ወይም ወራሾ በዓይነት ለመካፈል የሚቻል ሆኖ ከመካከላቸው አንዱ ባል ወይም ሚስት ወይም አንደኛው ወራሽ ብቻ የግድ ንብረቱ ሊሸጥ ይገባል በማለት ሲጠይቅ ንብረቱ በዓይነት መካፈል እየቻለ በአንድ ሰው መቃወሚያ ብቻ እንዲሸጥ የሚደረገው አሰራር እንዴት ይታያል? የሚገባው ፍትሀዊ ትዕዛዝ ምን ሊሆን ይገባል ?
8. በፍ/ር ክርክር ሂደት ያልተጠቀሰ የንብረት አይነት ወይም የንብረት ብዛት ወይም የይዞታ ስፋት አንደኛው ወገን መቃወሚያ ባነሳ ጊዜ ክርክር ማስተናገድ ጋር ተያይዘው ለአፈፃፀም የሚያ ስቸግሩ ትዕዛዞች እንዴት ይፈታሉ ? ወይም ይስተናገዳሉ?
9. በአንድ ንብረት ላይ ክርክር ተደርጎ የፍርድ ባለመብትና ባለዕዳ ተለይተው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ በሂደቱ ይገባኛል ወይም መብት አለኝ የሚለው ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ለፍ/ቤት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አቅርቦ ሳይከራከር የንብረት ሽያጭ ገንዘብ ከፍርድ ባለእዳ እና ባለመብት ተራፊ መሆን አለመሆን ሳይጣራ ከሌሎች ፍ/ቤቶችና ችሎቶች የሚመጡ ትእዛዞች እንዴት ይስተናገዳሉ? እንዲህ ዓይነት ችግር በመመሪያ ሊሸፈን ይችላል?
10. የፍ/ር ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ጊዜ በማስረጃ ያልተደገፈ የይዞታ ስፋት ላይ ክርክር አድረገው ካስወሰኑ በኋላ በአፈፃፀም ጊዜ በቦታው ስኬድ ይዞታው በማይገኝበት ጊዜ የፍ/አፈፃፀም የሚገጥመውን ተግዳሮቶች እንዴት በመመሪያ ማስደገፍ ይቻላል?
11. የፍ/ር ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ጊዜ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የቤት ቁጥር ብቻ ጠቅሰው ተከራክረው ከዚህ ቤት ቁጥር ግቢ ውስጥ ያሉ ቤቶች ሁኔታና ቁጥር እና የይዞታ ስፋት በአፈፃፀም ጊዜ አከራካሪ ሆኖ ሲነሳ በምን መልኩ መፍታት ይቻላል፣የክስና ክርክር አቀራረብ አፈጻጸምን ታሳቢ ማድረግ እንዲችል ፍርድ ቤቶች ምን ዓይነት የማሻሻያ ተግባራትን ማከናወን ይገባቸዋል-- ምሳሌ በክስ አመሰራረት ጊዜ... አቤቱታ እንዲሻሻል ማስገደድ የመሰለ...

12. ፍርድ ለማስፈፀም ተሽከርካሪ ተይዞ ወደ መኪና ማሳደሪያ በማስገባት ከሀራጅ በፊት የግምትና የጉብኝት ተግባር ማከናወን ግድ ነው። ይሁንና የፍ/ባለዕዳ አቤቱታ ለፍ/ቤት በማቅረብ ፍርድ ቤቶች ፍርድ እንዳይፈጸም ዕግድ ይሰጣሉ።አፈጻጸሙ መቆሙን ተከትለው የፍርድ ባለዕዳዎች ተሽከርካሪ እንዲለቀቅላቸው የፍርድ አፈጻጸምን ይጠይቃሉ።ተሽከርካሪው ባለበት የጥበቃ ቦታ መቆየት አለበት ወይስ ሊለቀቅለት ይገባል? ።በሌላ አነጋገር አፈጻጸም ለጊዜው ታገደ ማለት ተሽከርካሪው ይለቀቅ ማለት ነው ወይ ?